  

# የካቲት 12 የሰማዕታት ቀን

አገራችን ኢትዮጵያ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ ከቅርብ ጎረቤቶችና ከሩቅ ትንኮሳ ሲካሄድባት በቆራጥ መስዋዕትነት ጠላቶቿን ድል እያደረገች እነሆ እስከዛሬ ነጻነቷን አስከብራ ኖራለች።

የዛሬ 78 ዓመት በ1928 ዓ.ም ፋሺስት ኢጣሊያ በዳግማዊ አፄ ምኒሊክ አመራር የደረሰባትን ሽንፈት ለመበቀል ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን ታጥቃ በአውሮፕላን በታንክና በመርዝ ጢስ በመጠቀም ተንደርድራ አዲስ አበባን ተቆጣጠረች። ይህ ሲሆን የኢትዮጵያ ልጆች በየአካባቢያቸው የጎበዝ አለቃ መርጠው ጠላት ሰላም ተነስቶ እንደተቅበዘበዘ ለአምስት ዓመት ብቻ በየከተሞች ተወስኖ እንዲቆይ አድርገውታል።

በአዲስ አበባ የፋሺስት ሃይል በሕዝብ ላይ የሚያደርሰውን በደል አይተው ህሊናቸው እጅግ የቆረቆራቸው ሞገስ አስገዶምና አብርሃም ደቦጭ የተባሉ ወጣት ኢትዮጵያውያን የሙሶሊኒ ቀኝ እጅ የነበረውና ኢትዮጵያን እንዲያስተዳድር የተላከውን ሩዶልፍ ግራዚያኒን ለመግደል የወረወሩት ቦምብ ሳይገድለው ቀረ። ግን ክፉኛ ቆሰለ። ሆኖም በድርጊቱ እጅግ የተበሳጨው ግራዚያኒ ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ የተባሉትን የፋሺስት ጦር ጨካኝ ቡድን በአዲስ አበባ ሕዝብ ላይ አዘመተ። በዚህች በዛሬዋ ዕለት በ 1929 ዓ.ም እስከ የካቲት 14 ቀን በሶስት ቀናት ብቻ **30000** (ሠላሳ ሺህ) የሚሆን ሕዝብ ተጨፈጨፈ። ጭፍጨፋውም በርሸና፤ በስቅላትና በእሳት በማቃጠል ነበር።

አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል ሕዝብ በፋሺስት ሀይል እንዳይገዛ ያወገዙት አባቶች ያለርህራሄ ተረሸነዋል። በደብረ ሊባኖስ ይገኙ የነበሩ **300** (ሶስት መቶ) መነኮሳት በግፍ ተጨፍጭፈዋል። ከዚህም በተጨማሪ በሺህ የሚቆጠሩ ህዝቦች በአዲስ አበባና ከዚያም ውጭ በሚገኙ እሥር ቤቶች ተወርውረው እንዲማቅቁ ተደርጓል። ይህን ሁሉ በደል የፈጸመው ግራዚያኒ እ.አ.አ. በ**1948** ዓ.ም በዓለም ጦር ፍርድ ቤት ቀርቦ በኢትዮጵያውያንና በሊቢያውያን የፈጸመው ግፍ በማስረጃ በመረጋገጡ ለ19 ዓመት በጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ተፈርዶበት ወደ ወህኒ ቤት ተወርውሮ ከሁለት ዓመት እሥራት በሁዋላ ተፈቶ ደብዛውን አጥፍቶ ኖሯል። ግራዚያኒ ያን ሁሉ ጭፍጨፋ በአካሄደ በ76

ዓመቱ እ.አ.አ. ነሐሴ 11 ቀን 2012 በሮም አጠገብ በምትገኝ መንደር የኢጣሊያ መንግሥት ተወካይና የቫቲካን ተጠሪ ባሉበት በታላቅ ስነስርዓት የተሠራለት ሃውልት ተመርቋል። የንጹሃንን ደም በከንቱ ያፈሰሰ የጦር ወንጀለኛ እንደ ጀግና ተቆጥሮ ክብር እንዲሰጠው መደረጉ ለሰው ልጅ ደህንነት የሚቆረቆርን ሁሉ አሳዝኗል አስገርሟል። ይህ ድርጊት እንዲቀለበስ በአለም ዙሪያ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው።

በዚህ አጋማሚ ፋሺስት ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ በፈጸማቸው የጦር ወንጀል ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሕዝብ መጨፍጨፉንና እንዲሁም ከ2000 በላይ ቤተክርስቲያናትና ከ500000 (አምስት መቶ ሺህ) በላይ ቤት መቃጠሉን ማስታወስ ያስፈልጋል።

ማስታወስ ብቻ ሳይሆን ተገቢው የጦር ካሣ ለሀገራችን እንዲሰጥና ቫቲካንና የኢጣሊያ መንግሥት ይቅርታ እንዲጠይቁ ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

ስለዚህ ጉዳይ ይበልጥ መረጃ ለማግኘት www.globalallianceforEthiopia.org የሚባለውን ድህረገጽ መጎብኘት ይቻላል።

በዚህ በቶሮንቶም የመኢአድ የድጋፍ ሠጭ ድርጅት በጠራው የሰማዕታቱ የመጀመሪያ መዘከሪያ ዝግጅት ላይ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከታች በተጠቀሰው አድራሻ ተገኝተው የዝክሩ ተካፋዮች እንደሚሆኑ ይጠበቃል።

**427 Bloor St. West (St. Paul's United Church)**

**Saturday, February 22, 2014**

**5:00 p.m. – 7፡00 p.m.**

በሚቀጥለው ዓመት የሰማዕታት ቀኑን ሰፋ ባለና በደማቅ መልክ ለመዘከር ዕቅድ መያዙም ታውቋል።

የኢትዮጵያ ጠላቶችና ወኪሎቻቸው ይወድማሉ!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!